# ታየ ቶላ

***ታሪካዊ ልብ ወለድ***

የቄስ ተማሪ ቤት ጉዋደኞቹ ሆኑ የአስኩዋላ የልጅነት የትምህርት ቤት ጉዋደኞቹ ሁሉም ትዝታቸዉ ደግነቱና ሩህሩህነቱ ነዉ። አርሲ ዉስጥ ከአሰላ ከተማ ትንሽ ራቅ ብላ ከምትገኝ መንደር መወለዱን ብዙዎች ይናገራሉ። የመንደሩዋን ስም ግን የሚነግረኝ በዉል አላገኘሁም።

የልጅ አዋቂም ነበረ የሚሉ አሉ። የክፍል ጉዋደኞቹ እንደሱ ኦሮሞዎች፤ አማርኛ አጎላድፈዉ ሲናገሩ ሲሳቀባቸዉ፤የአፍ መፍቻ ቋዋንቋዋችዉ ስላልሆነ እንደሆነ በጥሞና ማስረዳት እንጂ፤ እንደ አንዳንዶቹ በዘር የተመሰረተ ስድብና ጥላቻን አይጠቀምም ይላሉ። እንዲያዉም፤ የሸሬዉን ተወላጅ መምህር አሊ፤ የመንዝ ተወላጁ መምህር ሹመት አቤታቸዉ እያኖሩ የሚያስተምሩዋቸዉን ኦሮሞ ተማሪዎች በምሳሌነት እየሰጠ፤ኢትዮጵያዊነታችንንና ሰብእነታችንን ያሳይ ነበር ይላሉ። እዉነትም የልጅ አዋቂ። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አቋዋርጦ ደብረ ዘይት የሄደዉ በአብዮቱ ዋዜማ ነበር።

እኔ ታየ ቶላን ያገኘሁት አየር ወለድ ተቀጥሮ ደብረዘይት ሲሰለጥን አልነበረም። እሱ ሲገባ እኔ ለቅቄያለሁ። አስመራ በሁዋላ በግዳጅ ተሰማርቶ ነዉ ያገኘሁት። ደብረዘይትም አብረዉት የሰለጠኑት እንደሚናገሩት፤ በልጅነቱ ያነሆለለዉ ኢትዮጵያዊ አባዜ የበለጠ የተጠናከረበት፤ በከተማይቱ ድሆችና በባለጸጎች መካከል ያየዉ የኑሮ ልዩነት እንደሚጎረብጠዉ ያስታዉሳሉ። አንድ ጉዋደኛዉማ ታየ ቶላ ቡና ቤት ገብቶ ለሴት ኮማሪቶች የሚያሳየዉ ክብርና ፍቅር ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ለሴቶቹ ለራሳቸዉ ሳይቀር ደብረዘይትን ለቆ አስመራ ሲሄድ እንባ በእንባ የተራጩበትን ወቅት በሃዘንም በኩራትም ያስታዉሰዋል።

አንዳንድ ሰዉን በመጀመሪያ ስሙ ብቻ መጥራት የልብ አያደርስም። ከነአባቱ ስም ፈርጠም አድርጎ መጥራት ያስፈልጋል። ታየ ቶላን ታየ ብቻ ብሎ የሚጠራዉ አላጋጠመኝም። ታየ ቶላ እንጂ።

ታየ ቶላ ቆፍጣና ወታደር ነበር። ለስላሳ ልብ ቢኖረዉም ዉጩ ሸካራ ነበር። አይኖቹ ፈጣጣና አንዳንዴ ደም የሚለብሱ ነበሩ። በተለይም ሲናደድ። ሰዉነቱ ደርባባና ሙሉ፤ ቀለሙ የአበሻ ጥቁር፤ ቁመቱ መካከለኛ ነበር።የሲጋራ ጢስ ሊያወይባቸዉ ያልቻሉ ነጫጭ ጥርሶች ነበሩት። ታዲያ ምን ያደርጋል በነበረ አለቀ።

ከታየ ቶላ ጋር ብዙ ብዙ ጦርነቶች አብረን ዘምተናል። በጥይት አረር ተደጋግሞ ሲፈተን ምስክር ነበርኩ። ለዚህም ነው ትዝታው ዛሬም አልጠፋ ብሎኝ ያለው። በደቀመሃሪ፤ በአፋቤት፤ በበለዛ፤ በባሬንቱ፤ በአላበረድ፤ በመአሚደ፤ በከረንና በናቅፋ የጦር ግምባሮች አብረን ውለናል። ባለ ሌላ ማእረግ ቢሆንም፤ ጠሩ ታየ ቶላን በመሪነትና በአራያነት ይከተለው ነበር። ደከመኝ፤ ሰለቸኝ፤ የማይል የጀግነነትና የጽኑነት ቁንጮ ነበር።

ታየ ቶላን ቀስ በቀስ የሚያበግነው ግን የደርግ አምባገነንነትና መላ ቢስነት ቅጥ እያጣ ሲሄድ ነበር። ስልጣኑን ለህዝብ አላስረክብም ማለቱ አንሶ (እሽ እሱም ይሁን አገሪቱ ከፍተኛ ጦርነት ላይ ነች) ጦርነቱን ራሱን ያለስልት፤ መንግስቱ ሀይለማርያምና የ 50 አለቃ ለገሰ አሰፋው ሲያጨማልቁት ግን ታየ ቶላ ልቡ ሸፈተ። የሻብያ አመጸኞችና የወያኔ አስገንጣዮች የቀን ጉዳይ ነው እንጂ እንደሚያሸንፉ በግልጽ ታየው። በጣም አምርሮ አዘኑ- ላገሩ ለኢትዮጵያ፤ ብርቅየና ብልህ ልጆች እንደሌሉዋት በማንም ዱርየ ገመናዋ ፈተው ብሎ የአለም መሳቂያ ስትሆን።

ከመሰል አየር ወለድ ጉዋደቹ ጋር ከጦርነት እረፍት ቀበሮ ጉድጉዋድ ውስጥ ረጅም ውይይት አደረግን። ብዙዎቹ ጉዋዶች ወያኔና ሻብያን ከደርግ ጋር ሆኖ ማሸነፍና ላገራችን ደሞክራሲያዊ ህዝባዊ መንግስት ለማምጣት አይቻልም ብለን ደመደምን። አንዳንድ ሃሞተቢሶች ለሻብያ እጃችን ለመስጠት አልዳዳንም። ራሳችን እናጠፋለን እንጂ ጨርሶ የማይሞከር ብቻ ሳይሆን የማይታሰብም ነበር።

በርካታዎቹ፤ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊትን አሲምባ ለመቀላቀልና አገራዊ ትግሉን ለመግፋት ወሰኑ። ታየ ቶላና እኔ ግን ደርግ ውስጥ ቀርተን መንግስቱንና ለገሰን በአድማ ከስልጣን ለመገልበጥና ስልጣኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማስረከብ ጸንተን ወሰንን። መሰነባበቻችን ሲቃረብ ሆዳችን ባር ባር ይለው ገባ። "ሁለታችን ብቻ ተለይተን ስንቀርና የጠፉት ጉዋደኞች መሆናችንን ስለሚያውቁ አለቆቻችን ችግር አይፈጥሩብን ይሆን" እያልን ሃሳብ ገባን። ባወጣው ያውጣው ብለን በመለያያችን ምሽት ተላቅሰን ተሰነባበትን። ከሻብያ ጋር የሚደረገው ጦርነት ፋታም ስላልሰጠ፤ ብዙም ጥርጣሬ ውስጥ አልወደቅነም።

በዚህ ጊዜ ታየ ቶላ ሁለት ገጠመኞቹ ትዝ ይሉኛል። አንደኛው አዲስ ወታደር ምልምሎችን ጊዜያዊ አሰልጣኝ ሆኖ ተመድቦ ያየሁትን ነው። ታየ ቶላ ቀደም ብየ እንዳልኩት ውጩ ሽካራ ነው። አንዱን አዲስ ምልምል የኮማንዶ ትምህርት አንገቱን አንቆ ሲያሰለጥነው ወጣቱ የሞተ ይመስለዋል። "በቃኝ፤ ልቀቀኝ፤ ወታደርነቱ ይቅርብኝ" ወጣቱ ማለት ሲጀምር ታየ ቶላ ይበልጥ ሲቃ ይይዘዋል። ትምህርቱን ወጣቱን እየጎተተ ማስተማር ሲቀጥልና ወጣቱም ሲርበተበት ገላጋይ መሀል ገብቶ ሰላም ይፈጥራል። ታየ ቶላ አይኖቹ ደም ለብሰው "ሻብያ እንዲህ

እያላገጡብን፤ እና ደግሞ ለስላሳ ስልጡኖችን እናስመርቅ ትላላችሁ" ብሎ ሁላችንም ላይ ቡዋረቀብን። የታየ ቶላ የአገር ፍቅር መጠን አልነበረውም።

ሌላው ገጠመኝ ደግሞ ደቀመሃሪ መንገድ ላይ ሻብያ ላይ ያደረግነው ደፈጣ ነው። የሻብያ ወታደር በሶስት ትላልቅ መኪና ከደቀመሃሪ ወደ አስመራ እንደሚንቀሳቀስ ስለሰማን አንድ ጠንካራ ስክዋድ ለደፈጣ ይመደባል። ስክዋዱ ኮረብታዎችን ይዞ በመጠባበቅ ላይ እያለ ታየ ቶላ ወደ ባቡር መንገዱ ሲወርድ እናየዋለን። ቀጥሎ ድልድዩ ስር ሲገባ አየነውና "ምን ሊያደርግ ነው" ብለን ስንገረም ደፈጣውን ያልጠረጠረ የሻብያ ጦር ቀጠናችን ውስጥ ተቃረበ። ይህንን ያየው ታየ ቶላ ለካ ሊጸዳዳ  ኑሮ ድልድዩ ስር የገባው፤ ሱሪውን እያጠባበቀ ወደ አቅራቢያው ኮረብታ ሲሮጥ ሻብያ ያይና የሽሽት ተኩስ እየተኮሰ እግሬን አውጭኝ ሩጫ ይሮጣል።

ታየ ቶላ ጉደኛ ነው።በሁዋላ ራሱም ለጉድ የፈጠረኝ ነኝ ይል ነበር ይላሉ። እኛም አመጽ ማስተባበር አቅቶን፤ ሻብያም በእኛ ወገን ያመራር ጉድለት ጉልበት እያገኘ የሰሜኑ ጦርነት እየተበላሸ ሄደ። ናቅፋ ጦርነት ላይ ሙዋሂቴን ክፉኛ ተመትቼ በጡረታ አዲስ አበባ ስመለስ፤ ከታየ ቶላ ጋር ለረጅም ጊዜ ተለያየን። በሁዋላ እንዳጫወተኝ እነሁሴን አህመድና ጀኔራል ጥላሁን ጠፉን አጋፍጠው ሲሸሹ፤ ታየ ቶላ የተበተነው ጦር መሪ ሆኖ መልሶ ማሰባሰብ እያደረገ በሻብያ ላይ መጠነኛ ጉዳት አድርሶ ነበረ። ዳሩ ግን የጦሩ ሞራል አንዴ ስለወደቀ በስፋት እጅ መስጠት ለዚያውም ህይወቱ ላይተርፍና መረፍረፍ ሆነ የጦሩ እጣ።

ሻብያ እጁን ይዞ ታየ ቶላን ለሚሰጣት ሽልማት ስታዘጋጅ፤ ታየ ቶላ ቦላሌ ሱሪውን ቁምጣ አድርጎ፤ የበረሃ ጫማ ከሞተ የሻብያ ታጣቂ ወስዶና ታጣፊ ክላሽኑን በፊልድ ጃኬቱ ሸጉጦ በ 3 ኮዳ ወሃ ርዳታ ጉዞውን በበረሃ አቀራርጦ፤ በ4ኛ ቀኑ ከሰላ ላይ ለሱዳን እጁን ይሰጣል። 1 አመት ያህል ሱዳን እየተልፈሰፈሰ ከኖረ በሁዋላ ወያኔ ምህረት ስታደርግ አዲስ አበባ ተመልሶ ጉዋዴን ሳይሞት አይኑን አየሁት። አሜሪካ የሚኖሩ ጉዋደኞቻችንን ባደረጉለት የገንዘብ ርዳታ ታየ ቶላ አንዲት ታክሲ ገዝቶ በታክሲ ሾፌርነት ሲሰራ የግንቦቱ 1997 ምርጫ ከተፍ ይላል።

ወድቆ የነበረው ሞራላችን እንደገና አንሰራራ። በተለይ ታየ ቶላማ መጀመሪያ ህብረትን አዲስ አበባ ውስጥ ለመደገፍ ከፍተኛ ጥረት አደረገ፤ አመርቂ ስራ እንዳልሰሩ ሲያይ ወያኔ መውደቅ ስላለበት፤ ቅንጅትን በስፋት ያግዝ ነበር። በታላቁ ሰላማዊ ሰልፍ ጊዜ አሮጊቶችን ወደ መስቀል አደባባይ በነጻ በማመላለስ፤ መፈክሮችን በመጫንና በመሳሰለው ብዙ ረዳ።በምርጫው ቀንም ለተሰላፊው ከራሱ ኪስ የሚበላና የሚጠጣ እየገዛ ብዙ ረድቶኣል።

የታየ ቶላን ለዚህ ዳግማዊ ትግል መብቃት ሳስበዉ፤ ይህን ሳያዩ የተሰዉት ጉዋዶቻችን እነ አበጀ፤ዘውዴ፤ጌትነት፤ህብስቱ፤ወንድማገኝ...እልፍ አእላፉ ትዝ አሉኝ።

ወያኔ ምርጫዉን አጭበርብሮ ፓርላማዉን ሲከፍት ህዝቡ ተቃዉሞ ሲያሰማ ታየ ቶላም ታክሲ ነጅዎችን በማስተባበር አድማዉን ተቀላቅሎአል። ከሚኖርበት ከቂርቆስ እንዳያፍኑት ታክሲዉን ሰሜን ሆቴል እያሳደረ ትግሉን ለመግፋት ሲሞክር በጠቁዋሚ ተይዞ እነሆ እስር ቤት ከወረደ አመት ተመንፈቅ ሆነዉ። ለነገሩ የንግድ ፈቃዱን ወያኔ አግዶት ስለነበረ ስራም ሊሰራ አይቻለዉም ነበር።

አንዴ ልጠይቀዉ እስር ቤት ስሄድ በህልሙ ያየዉን ነገረኝ። "ጎንደር ከኢሃፓዎች ጋር አብሬ የተሰለፍኩ ይመስለኛል። ጭልጋ አካባቢ ሳይሆን አይቀርም። እንዲያዉም ማንኮይት የምትባል ትንሽ የገጠር ከተማ ትመስለኛለች" አለ። ያለወትሮዉ በጣም ጥልቅ ሃዘን ገባዉና እኔንም አሳሰበኝ። ቀጠለ - "ጠላ የምጠጣበት ቤት ገብቼ አንድ ዋምራ ጠላ ስጠጣ ያለወትሮዉ ጠላዉ እንደ ኮሶ መረረኝ" አለና ፊቱን አኮማተረ። "ጠላዉን አልጨረስኩትም፤ አዙሮኝ ወደቅሁና በድንጋጤ ከንቅልፌ ባንኜ ተነሳሁ" አለኝና በረጅሙ ተነፈሰ።

የወያኔ የወህኒ ፖሊስ የጉብኝት ሰአት ማለቁን ሊነግረኝ ወደኔ አግጣጫ ሲመጣ፤ ታየ ቶላ እንዲህ አለ። "መርዝ ያጠጡኝ ይመስለኛል፤ ደርግ ይሁን ወያኔ አላወቅሁም፤ ስለ ቀብሬ ስነስርአት ግን በሚቀጥለዉ ቀን ስትመጣ እንጫወታለን" ብሎኝ ተለያየን።

የጀግናው የመጨረሻ እስትንፋስ።

*ከሃይሌ አባይ*